# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ልዩ ዕትም ቁጥር 1 የካቲት ፲፪ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.

## <u>የካቲት ለኢትዮጵያ አንድነት</u>

(የካቲት 12 የሰማዕታት ቀን 81ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ)

የካቲት 12 መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሐዘን ልብስ ለብሶ ሐዘን የሚቀመጥበት ቀን ነው። አረመኔው የኢጣልያ ፋሺስቶች በ1929 ዓ. ም. በዚች ዕለት ጀምሮ ለሦስት ቀናት የአዲስ አበባን ሕዝብ ያለአንዳች ምሕረት ፈጁት። ምክንያት የሆናቸው የግራዚያኒ መቍሰል ነበረ። የዓይን ምስክሮች እንደመዘገቡት፥ ገዳዮቹም ተገዳዮቹም የተወሰኑ ሰዎች አልነበሩም። በአዲስ አበባ የነበረ ማንኛውም ኢጣሊያዊ አዲስ አበባ የነበረውን ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ መንገድ ላይ ካገኘው ይገድለዋል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ስንል ሕፃናት፣ ሴቶችን፣ አሮጊቶችን፣ እርጉዞችን፣ ሽማግሌዎችን፣ ለማኞችን እንኳ አልማሩም ማለታችን ነው። ለግድያው ወታደሮቹ የታጠቁት መሣሪያ ነበራቸው። መንገድ ሠሪዎቹ ግን ሕዝቡን የጨፈጨፉት በእጃቸው ውስጥ በነበረው ዶማ፣ አካፋ፣ መጥረቢያ፣ ድጅኖ ነበር። እመንገድ ላይ ያልተገኘውን ፍለጋ ብዙ ቤቶችን ሰው በውስጣቸው እንዳለ በእሳት አጋዩዋቸው። አዲስ አበባ በነዚህ ሦስት ቀናት ውስጥ ሠላሳ ሺ የሚሆኑ ነባሮቿንና ከየአገር ቤቱ ለጉዳይ የመጡትን አጥታለች። በእነዚህ ዕለታት ሟች እንጂ ቀባሪ አልነበረም። ጣሊያኖቹ የሬሳውን ሽታ ስላልቻሉት ቤንዚን እያርከፈከፉ አቃጠሉት።

ግራዚያኒን ያቆሰሉት አብርሃ ደቦጭ እና ሞገስ አስገዶም ደብረ ሊባኖስ ተሸሽገው ይሆናል በማለት ገዳሚቷን ዘመቱባት። በምንኩስና፣ በተማሪነት፣ በተመጽዋች፣ በጠበሏ ተፈዋሽነት ተጠግተዋት ከነበሩት ውስጥ ሦስት ሺውን አጨዱቸው።

የካቲት 12 ጭፍጨፋ መንሥኤው ቀደም ብሎ የተጀመረው የአውሮፓውያን የሰው አገር የመጓጓት ስግብግብነት ነው። እስያንና አፍሪካን ሲሻሙ ኢትዮጵያ ቀርታቸው ነበር። እንዳይተዋት በመሬቷ ስብነት፣ በውሃዎቿ ብዛት፣ በባሕሮች ዳር መንጣለሏ፣ በአየሩዋ ለኑሮ ተስማሚነት ቡዳውን ዓይናቸውን ማረከው። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የሰው አገር ለመንጠቅ ለሕዝባቸው የሚሰጡት የጮሌ ምክንያት በሕዝባቸው ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ደካማውን ሕዝብ የሚወሩት፥ “የሚጻፍ ቋንቋ የሌላቸው፣ ራቁታቸውን የሚሄዱ ሰዎች ስለሆኑ፥ መጻፍና ማንበብ እናስተምራለን” እያሉ ነው ። ኢትዮጵያን ለመውረር ሲመጡ ይህ ምክንያት በሕዝባቸው ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም። ምክንያቱም ያገራቸው ምሁራን፣ ተመራማሪዎችና አገር ጎብኝዎች ከእነሱ ቀደም ብለው ኢትዮጵያ መጥተው ስለ አስደናቂ ብሔራዊ ትምህርት ያዩትንና የሰሙትን በሰፊው አሳትመው ተሸልመዋል። ለማስረጃ እንዲሆናቸው የጥንት የብራና መጻሕፍት በገፍ ሰብስበው ወስደው አሳይተዋል።

አሁን እንግዲህ የወረራ ዘዴ መለወጥ ነበረባቸው። መጀመሪያ ማእከላዊው መንግሥት ፈጥኖ የማይደርስበትን ክፍል እየሸረፉ መውሰድ ጀመሩ። እንግሊዝና ኢጣልያ ሱማሌን ወሰዱ፤ ፈረንሳይ ጅውቲን ወሰደች። ቀጥሎ አጼ ዮሐንስ የደርቡሽን ወረራ ለመመከት መተማ ሲዘምቱ ኢጣልያ "ኤርትራ" የሚል ስም ያወጣችላትን ክፍል ወስዳ፥ ወደ ማህል አገር ስትገፋ አድዋ ላይ ድባቅ ተመታች። ድሉ የመጀመሪያው የቅኝ ገዢዎች ሽንፈት፣ የመጀመሪያው የአፍሪካ ድል ተብሎ በዓለም ታሪክ ተመዘገበ።

ይህ ታሪክ ቅኝ ገዢዎችን እንዳዋረደና እንዳስደነገጠ ከእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስቴር ከሚስተር ዊንስቶን ቸርችል ቃል መረዳት ይቻላል። እንዲህ ይላል፤

> *On the 1st of March, 1896, the Battle of Adwa was fought and Italy, at the hands of Abyssinia, sustained a crushing defeat. Two results followed which affected other nations. First, a great blow had been struck at European prestige in North Africa. Second, the value of Italy as a factor in European politics was depreciated.*

> *የካቲት 23 ቀን፥ 1888 ዓ.ም. የዐድዋ ጦርነት ተካሄዶ፥ ኢጣልያ በኢትዮጵያውያን እጅ የሚያደቅ ሽንፈት ደረሰባት። (ሽንፈቱ) ሌሎች ሕዝቦችን የሚነኩ ሁለት ውጤቶች አስከተለ። አንደኛ፥ ሰሜን አፍሪካ ላይ የአውሮፓ ክብር ክፉኛ ተመታ። ሁለተኛ፥ የኢጣልያ ዋጋ በአውሮፓ ፖለቲካ መቈጠር ዝቅ አለ።*

ኢጣልያ በዐድዋ የደረሰባት ሽንፈትና መሳቂያ መሆን ሙሶሊኒን አስቆጣው። በሱ አስተያየት የኢጣልያ ክብር መመለስ አለበት። ክብሩ የተነካው ባለበት ተደፍሮ ሳይሆን ሊቀማ ሲመጣ በመደፈሩ መሆኑን ትንሺ ጭንቅላቱ ልትደርስበት አልቻለችም። አስመራ ላይ የጦር መሣሪያውን ከመረ። በግሎባል አሊያንስ ድረ ገጽ (http://www.globalallianceforethiopia.net) እንደተዘገበው 5,000 የመርዝ ቦምብ የክምሩ ክፍል ነበር። ሁሉንም በሰውና በከብት ላይ ከአየር አዘነበው። አንድ ሚሊዎን ሕዝብ፥ 14 ሚሊዮን ከብት ተቃጠለ። 525,000 ቤቶችን፥ 2,000 አብያተ ክርስቲያናትን የሳት እራት አደረጋቸው። ሙሶሎኒ፥ "ጦርነቱ ርኅራኄ አልባ" ይሆናል ያለውን ወታደሮቹ ቃል በቃል ፈጸሙለት። የጥንት ቅርሳ ቅርሶችን ዘረፏቸው።

ኢትዮጵያ የሕዝቦች ኅብረት (League of Nations) አባል ስለሆነች፥ ንጉሠ ነገሥቱ በአካል ተገኝተው አንድ የአባል አገር በአንዲት የአባል አገር ላይ የሚፈጽመውን ግፍ ለማስረዳት ጀኔቫ ለመሄድ ቢሞክሩ ስዊዘርላንድ ገለልተኛነቷን መጠበቅ ምክንያት አድርጋ የመግቢያ ፈቃድ ልትከለክላቸው ሞከረች። እንደምንም ብለው ገቡ። የመሣሪያና የዘይት መግዛት ማዕቀብ ተላለፈ። ባይተላለፍ ይሻል ነበር። የዘይት ጉዳይ ከሆነ፥ አሜሪካ በዚያን ጊዜ የሕዝቦች ኅብረት አባል ስላልነበረች ኢጣልያ የዘይት ችግር አልገጠማትም። መሣሪያም ቢሆን ኢትዮጵያን ለመውረር የሚበቃ ታመርት ነበር። ማዕቀቡ የጎዳው ኢትዮጵያን ነበር። የተገዛው መሣሪያ የጅውቲን ወደብ ማላፍ አልቻለም። ወታደሩ በ1935-41 ዓመተ ምሕረት ዐድዋ ላይ በ1888 ዓመተ ምሕረት በተዋጋበት መሣሪያ መዋጋት ነበረበት።

ኢጣልያ ከሂትለር ጀርመን ጋራ መሞዳሞድ ስትጀምር፥ እንግሊዝ ልታዳክማት ፈልጋ ወታደሮቿ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የስዊዝን ቦይ (Suez Canal) ከፈተችላት። የኢጣልያ ወታደሮች አልፈው ሲያልቁ፥ "በኢጣሊያ አንገት ላይ ማነቆ ጠመጠምኩባት" ብላ ፎከረች። ሙሶሊኒም፥ "በማዕቀቡ መሠረት ዘይት ብከለከል ኖሮ ጦርነቱ በጥቂት ወራት ያልቅ ነበር" አለ።

ለጊዜው ኢጣልያ አሸነፈች። የአሥር ዓመት ልጅና ባለሞያ ቦቅሰኛ ቦቅስ ገጥመው አሸናፊው ሲኩራራ የታየው፥ ባዶሊዮ ሚያዝያ 27 ቀን አዲስ አበባ ሲገባና ግራዚያኒ የካቲት 12 የአዲስ አበባን ሕዝብ የፈጀ ዕለት ብቻ ነው።

አሁን እንግዲህ የጣሊያን ገበሬዎችን ከለሙ የኢትዮጵያ መሬት ላይ ለማስፈር መንገድ መቀደድ ጀመሩ። ኤርትራንና ሱማሌላንድን "ጥንትም የኢትዮጵያ ክፍል ነበሩ" ብለው እንደጥንቱ የኢትዮጵያ ክፍል አደረጉና ለአስተዳደር አገሪቱን በቋንቋ አውራጃዎች ከፋፈሏት።

ከነፃነት ሌላ የማያውቅ ሕዝብ በአንድነት ተነሣ። ከአምስት ዓመት ትግል በኋላ ነፃነቱን ተቀዳጀ። ሆኖም በአምስቱ ዓመታት የግፍ አገዛዝ ወቅት ወራሪው ፋሽስት በግፍና በማስገደድ የደፈራት ሀገር ከሃዲና የእናት ጡት ነካሽ የሆኑትን ባንዳና ህወሓት የመሳሰሉ ሀገር በቀል አጥፊዎችን ወለደች። ኢትዮጵያ ቅዱስ መሬት ላይ ርኩስ ልጆች ተወለዱ። ሙሶሎኒ፥ "ጦርነቱ ርኅራኄ አልባ" ይሆናል ያለውንና ወታደሮቹ ቃል በቃል የፈጸሙለትን የአግዓዚ ወታደሮች አርቀው አምጥቀው ወሰዱት። የሚፈሩትን ሰው ቁልቁል ይሰቅሉታል፣ ጥፍሩን በጉጠት ይነቅሏቸዋል፣ እንደሰንጋ በሬ ያኰላሹታል።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ፋሺስቶችን ድባቅ መትተው ኢትዮጵያን ነፃ እንዳወጡ የረከሱ ልጆቻቸውንም ድባቅ መትተው ሕዝቡን ነፃ ማውጣት ይጠበቅባቸዋል።

***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** የካቲት 12 የሰማዕታት ቀንን ስናስታውስ ኢትዮጵያ ሀገራችን በልጆቿ ደምና አጥንት እንደተገነባች እያስገነዘብን ነው። የኢትዮጵያችን ለም መሬቶችና በረሃዎቿ፣ ደንና ዱር አራዊቶች፣ አዕዋፍ፣ ወንዞችና ተራሮቿ፣ የቀንድና የጋማ ከብቶቿ፣ ዛሬ ያለው ሀገሬን ያለው ሕዝቧ ለሀገር አንድነትና ለግዛቷ ክብር አጥንታቸውን በከሰከሱ፣ ደማቸውን ባፈሰሱ የመተማ፣ የዶጋሌ፣ ዐድዋ፣ የካቲት 12፣ ማይጨው እና ሌሎች ሰማዕታት ደም ውስጣቸው አለ።

ሀገራችን በተለያየ ወቅት የገጠሟት ሀገር አጥፊ፣ ታሪክ አውዳሚ፣ ሕዝብ ገዳይ አገዛዞችና ወረራዎች አስተናግዳለች። ከነዚህም አንደኛው ሀገሪቷን ለ27 ዓመታት በመንግስትነት ተቆጣጥሮ እየበላትና እያሽመደመዳት ያለው የወያኔ/ህወሓት አገዛዝና የጥፋት ዘመን ነው። ይህ ሀገር አጥፊ ዘረኛ አገዛዝ ተሻለው የማይባል መሠሪና የጥፋት መጨረሻውን ሀገራችን ላይ በተጠናከረ መልኩ ሊያሳርፍ ሰሞኑን ያወጣው የአስቸካይ ጊዜ አዋጅ ከበቂ በላይ መስካሪ ነው። የህወሓት አገዛዝ ምን ጊዜም ቢሆን ሀገሪቷን ለማጥፋት ሕዝቧን ለመፍጀት የመጣብን የጥፋት ዘመን መሆኑ ከአእምሯችን ሊፋቅ አይገባውም። በልማትና ዕድገት ስም፣ በዴሞክራሲ ስም ሀገር ዘርፏል፣

**ዜጎቻችንን ጨፍጭፏል። ይህ የማደናገሪያና የማታለያ ጭምብሉ ከተገለጠ የከራረመ ቢሆንም ከአለፉት ሦስት ዓመት ወዲህ ይበልጡን እየከፋና እርቃኑን እየወጣ ይታያል።**

**ዛሬ ወያኔ ህወሓት ኢትዮጵያን እያጭበረበረ ሊገዛ እንደማይችል ምስጋና ይገባቸውና የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የደቡብ ወገኖቻችን፣ የምዕራብ ጋምቤላዎች፣ የምሥራቅ ወገኖቻችን፣ በጥቅሉ ሕዝባችን እያሳየ ያለው እምቢተኝነት ምስክር ነው። ይህ በሕዝብ የተጠላ አገዛዝ መጠላቱን ተገንዝቦ መትረየሱን እያቀባበለ፣ ታንኩን እያሞቀ ይገኛል። "አጥፍቶ ሊጠፋ"። ምኞትና ቅዠት ይሆንበታል እንጂ ሀገርና ሕዝብ ኖረው እሱ ይጠፋል። ለወያኔ/ህወሓት መጥፋት የሚከፈለው መስዋዕትነት ክቡር ብቻ ሳይሆን የክቡር ክቡር መሆኑን የተገነዘበው ሕዝባችንና ልጆቹ ለምዬ ኢትዮጵያ የሚያፈሱት ደም፣ የሚከሰክሱት አጥንት ክብር ነው። ከአፄ ዮሐንስ፣ ከአፄ ቴዎድሮስ፣ ከአሉላ አባ ነጋ ተጋድሎ፣ ከአፄ ምንሊክ ዐድዋ፣ ከነበላይ ዘለቀ፣ ከአርበኞቻችን፣ ከአቡነ ጴጥሮስ ታሪክና መስዋዕትነት የማይነጥፍ ትምህርት ቀስሟልና በተጀመረው ሀገር አድን ተጋድሎ የመጨረሻው ግባአተ መሬት ለወያኔ/ህወሓት እንደሚሆን አንጠራጠርም።**

***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** **የየካቲት 12 ሰማዕታትን ስንዘክር ለሀገራችን ዘላለማዊነትና ለሕዝባችን አንድነት እየተከፈለ ያለውን መስዋዕትነት እያከበርንና እየዘከርን ነው። ዛሬ ለኢትዮጵያ ነፃነት ሰዉ ብቻ ሳይሆን አዕዋፍ እየዘመሩ፣ የዱር አራዊት እየጨፈሩ፣ ወንዞች እያጓሩ፣ አለሁልሽ ኢትዮጵያዬ እያሉነውና የተቀጣጠለው ሕዝባዊ ዓመጽ በድል አድራጊነት እንደሚጠናቀቅ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።**

**አሳፋሪው የወያኔና ኢሕአዴግ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ህወሓትን ኮማ ውስጥ ያስገባ የጣር ጩኸት ነው እንላለን። አልወጣ ያለ የወያኔ ነፍስ በጣሩም ይቃዣልና ፍታት አልባው ሞት የወያኔን ደጃፍ አንኳኩቷል። ወያኔ አጥፍቶ ሳይሆን ቃዥቶ ይጠፋል እንላለን።**

**የየካቲት ሰማዕታት ለኢትዮጵያ አንድነት!!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"**
**የካቲት 12 ቀን 2010 ዓ.ም. (February 18, 2018)**

**ማሳሰቢያ ፡**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachen